የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

## በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

(ከመስከረም 20- 27/2017 ዓ.ም)
(October 01- 07/2024)

**1.ለጅምላና ለችርቻሮ ንግድ ሥራ 71 ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ፍላጎት ማሳየታቸው ተነገረ**

***Reporter: October 6, 2024***

የውጭ ባለሀብቶች በአገር ውስጥ የጅምላና የችርቻሮ ንግድ እንዲሰማሩ የሚፈቅድ መመርያ ይፋ ከተደረገ በኋላ፣ ከሐምሌ ወር ጀምሮ 71 ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ፍላጎት ማሳየታቸውንና 20 ያህሉ ፈቃድ ማውጣታቸው ተገለጸ::

ከሁለት ወራት በፊት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመሩት የኢንቨስትመንት ቦርድ፣ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ይፈቀዱ የነበሩ የንግድ ሥራዎች ለውጭ ኩባንያዎች እንዲከፈቱ መወሰኑ ይታወሳል::

የውጭ ባለሀብቶች በጅምላና በችርቻሮ ገበያ እንዲሰማሩ የሚፈቅድ ሕግ ከወጣ በኋላ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምዝገባና ፈቃድ መስጠት ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ 21 ድርጅቶች ፈቃድ ማውጣታቸውን፣ 13 ድርጅቶች በችርቻሮ ገበያ ለመሰማራት፣ ወደ ውጭ ምርቶችን ለመላክ ደግሞ ስምንቱ ድርጅቶች መሆናቸውን የገለጹት፣ በኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከፍተኛ የፖሊሲና የሕግ ጉዳይ አማካሪ ሀብታሙ ስማቸው (ዶ/ር) ናቸው::

https://www.ethiopianreporter.com/134040/

**2.የኃይል አቅርቦት የተቋረጠበት የኢትዮ ጂቡቲ ባቡር ከጂቡቲ ኃይል ወስዶ አገልግሎት መጀመሩ ተገለጸ**

**Reporter:October 6, 2024**

የኢትዮ ጂቡቲ ባቡር የኤሌክትሪክ ኃይል ተሸካሚ መስመር ተዘርፎ ችግር ቢገጥመውም፣ ከጂቡቲ ኃይል ተወስዶ የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ማስቀጠሉን የኢትዮ ጂቡቲ ምድር ባቡር አስታወቀ::

ከቆቃ – ሁርሶ የተዘረጋው 230 ኪሎ ቮልት ጥምር የኃይል ማስተላለፊያ መስመር በአፋር ክልል አዋሽ ፈንታሌ ወረዳ አዋሽ አካባቢ በኃይል ተሸካሚ ምሰሶ ተሰርቆ አገልግሎት በመቋረጡ፣ ከጂቡቲ ኃይል ተወስዶ የባቡር አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ መደረጉ ተገልጿል::

የኢትዮ ጂቡቲ ምድር ባቡር ቺፍ ቴክኒካል ኦፊሰር አቶ ዳንኤል ኃይለ ሚካኤል ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ 230 ኪሎ ቮልት ጥምር ኃይል አስተላላፊ መስመሮች በተደጋጋሚ ይዘረፋሉ::

በተለይ ከባቡሩ መስመር ጋር የሚገናኘው የአይሻ መስመር ኃይል ተሸካሚ ምሰሶ መውደቁን ገልጸው፣ ብልሽቱን ለማስተካከል ለአንድ ቀን ሙከራ መደረጉን ተናግረዋል::

የአይሻ አካባቢ ለጂቡቲ ቅርብ በመሆኑ መስመሩን ከጂቡቲ ጋር በማገናኘት ኃይል እንዲያገኝ መደረጉን አስረድተው፣ የባቡር መስመሩ ወዲያው አገልግሎት መስጠት መጀመሩን ገልጸዋል::

https://www.ethiopianreporter.com/134034/

**3. ልዩ መብት የተፈቀደላቸውን ጨምሮ አምራች ድርጅቶች የሚያስገቧቸው ግብዓቶች በውጭ ፍተሻ እንዲስተናገዱ ተፈቀደ**

**Reporter: October 6, 2024**

በጉምሩክ ኮሚሽን ልዩ መብት የተፈቀደላቸው ድርጅቶችን ጨምሮ 202 አምራች ድርጅቶች ለማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ለሚያስገቧቸው ግብዓቶችና የካፒታል ዕቃዎች በውጭ ፍተሻ እንዲስተናገዱ ተፈቀደ::

ሪፖርተር የተመለከተውና በጉምሩክ ኮሚሽነሩ አቶ ደበሌ ቃበታ ተፈርሞ ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የተመራው ሰርኩላር እንደሚያሳየው፣ የቅድሚያ አገልግሎትና የውጭ ፍተሻ አፈቃቀድና አፈጻጸም በኮሚሽነሩ ብቻ እየታየ ሲፈቀድ ቆይቷል::

የውጭ ፍተሻ ከጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ወይም ጣቢያዎች ውጪ በሕግ ወይም በኮሚሽኑ በተፈቀደ ቦታ የሚከናወን ሲሆን፣ ዲክላራሲዮኑ ከተከፈተበት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ውጪ በሌላ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወይም ጣቢያ የሚደረግ ፍተሻን ይጨምራል::

ከነሐሴ 2 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የውጭ ፍተሻ አፈቃቀድና አፈጻጸም በልዩ ሁኔታ በኮሚሽነሩ እየታየ እንደሚፈቀድ፣ ሆኖም ለአምራች ኢንዱስትሪው ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት ከመስጠት አኳያ የቅድሚያ አገልግሎት አሰጣጥና የውጭ ፍተሻ ማሻሻያ መደረጉ ታውቋል::

https://www.ethiopianreporter.com/134029/

**5. የኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢዎች እስከ አምስት ሚሊዮን ብር የፈቃድ ክፍያ እንዲከፍሉ የሚደነግግ መመርያ ወጣ**

**October 2, 2024**

የኢትዮጵያ ኮሙዩኒኬሽን ባለሥልጣን የኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢነት ፈቃድ የሚጠይቅ አካል፣ እስከ አምስት ሚሊዮን ብር የሚደርስ የፈቃድ ክፍያ እንዲፈጽም የሚጠይቅ መመርያ ወጣ::

በኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 መሠረት የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲን ጨምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ለቴሌኮሙዩኒኬሽን አገልግሎትና ለኢንፎርሜሽን አገልግሎት አቅርቦት የሚውሉ የቁጥርና የአድራሻ ሀብቶችን የማስተዳደርና የመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው የኮሙዩኒኬሽን ባለሥልጣን ባዘጋጀው የኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድና አስተዳደር ክፍያ መመርያ፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ለማቅረብ ፈቃድ የሚጠይቅ አመልካች የማመልከቻ 2,500 ብር፣ የፈቃድ አምስት ሚሊዮን ብር፣ እንዲሁም ከዓመታዊ አጠቃላይ ገቢው አንድ በመቶ የሚሆነውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ይጠበቅበታል::

https://www.ethiopianreporter.com/133996/

6. ***ሁለተኛው የቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ተካሄደ***

**ኢ.ዜ.አ፡ መስከረም 26/2017**

በድሬዳዋ በተካሄደው በሁለተኛው ምዕራፍ የቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ የቆላማ አካባቢዎችና መስኖ ሚኒስቴር የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች፣ የዓለም ባንክ ተወካዮች እና ፕሮጀክቱ የሚመለከታቸው የድሬዳዋ የካቢኔ አባላት ተገኝተዋል።

በዚሁ ወቅት በሚኒስቴሩ የቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ዋና አስተባባሪ አቶ ሰዒድ ኡመር እንዳሉት፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ የፕሮጀክቱ አተገባበር የአርብቶአደሩን ህይወት ከተረጂነት ለማላቀቅ የሚያግዙ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5248183

7. ***የማዕድን ዘርፉን ባለሙያዎች አቅም ለማሳደግ የሚሰራው ማህበር***

**Ethiopian: October 4, 2024**

የማዕድን ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት ቢሆንም፣ ሀገሪቱ ያላትን የማዕድን ሀብት ለይቶ አውቆ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውልና በሥርዓት እንዲመራ ከማድረግ አኳያ ብዙ እንዳልተሰራ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለዚህም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል ዋንኛው ዘርፉን በሥርዓትና በተቀናጀ መልኩ ለመምራት የሚችሉ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች አለመኖራቸው መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

እንደ ሀገር ዘርፉ ብዙም ያልተሰራበት እንደመሆኑ ልምድ ያካበቱ ብዙ ባለሙያዎች አለመኖራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ያሉትም ቢሆኑ በጽንስ ሃሳብ የቀሰሙትን እውቀት ወደ ተግባር ለመለወጥ ሲቸገሩ ይስተዋላል። የባለሙያው የብቃት ክፍተት ዘርፉ ባለሙያ እንዳይደገፍ ያደርገዋል፤ ይህም ክፍተቶች እንዲፈጠሩና ወጥ የሆነ የአሰራሩ ሥርዓት እንዳይኖር ምክንያት ይሆናል። ችግሩን ከሥር መሠረቱ ለመፍታት ልምድ ካላቸው ባለሙያዎች ጀማሪዎቹ ልምድና ተሞክሮ እንዲቀስሙ ማድረግ ላይ የሚሰራ የሙያ ማህበር እንዲኖር የግድ ይላል። ዶክተር ታረቀኝ ታደሰ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የጂኦሎጂ ተባባሪ ፕሮፌሰር፣ የኢትዮጵያ ጂኦሳይንስ ማዕድን ምህንድስና ማህበር ፕሬዚዳንት እና በጂኦሎጂና በማዕድን ዘርፍ አማካሪም ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ የጂኦሳይንስ ማዕድን ምህንድስና ማህበር የተመሰረተው እ.ኤ.አ 1992 ነው። አብዛኛዎቹ የማህበሩ አባላት በተለያዩ የሙያ ዘርፎች /በሥነ ምድር፣ በጂኦሎጂ ፣ በሃይድሮሎጂ፣ በማዕድን ፍለጋ እና በመሳሰሉት/ ላይ የሚሰሩ ናቸው። ማህበሩ በተለያዩ የሥነ ምድር ሙያዎች የሰለጠኑ፣ የተማሩ፣ በማዕድን ቁፋሮ ዲዛይን /ማይኒግ ኢንጂነሪንግ/ እንዲሁም በውሃ ላይ በአጠቃላይ በሥነ ምድር ጥናት የሚሰሩ ሳይንቲስቶችን፣ ተመራማሪዎችን፣ አስተማሪዎችንና ምሩቃንን አቅፎ ይዟል።

ማህበሩ በዋናነት የሙያ ማህበራትን ብቃት ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች ሲሰራ ቆይቷል። ስልጠናዎችን መስጠት፣ ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ኮንፍረንሶችን በማዘጋጀት ጥናታዊ ጽሑፎች እንዲቀርቡ በማድረግ ለዘርፉ ግብዓትና ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ ሥራዎችን ይሰራል። መንግሥትም ሆነ የዘርፉ ኃላፊዎች የሚያስፈልጓቸው ሙያዊ ጉዳዮች ሲኖሩ በሥነ ምድር ጥናት አንጋፋና የረጅም ዓመታት ልምድ ያላቸው ብዙ ባለሙያዎች ስላሉት ልምዳቸውንና እውቀታቸውን ያጋራል፤ ያማክራል።

https://press.et/?p=137913

**4. የፋይናንስ ተቋማት በሚሰጧቸው አገልግሎቶች ክፍያ ላይ ተጨማሪ ዕሴት ታክስ ማስከፈል ጀመሩ**

**Reporter: October 2, 2024**

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የመሰብሰብ ግዴታ ሳይኖርባቸው የቆዩት የፋይናንስ ተቋማት ከትናንት ጀምሮ በሚሰጧቸው አገልግሎቶች ላይ ተጨማሪ ዕሴት ታክስን በመጨመር አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን እያስታወቁ ነው፡፡

ከ21 ዓመታት በላይ በቆየው ነባሩ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ የፋይናንስ ተቋማት የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ሳይመለከታቸው የቆየ ቢሆንም በአዲሱ አዋጅ የፋይናንስ ተቋማት የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የመሰብሰብ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

ባንኮች ኢንሹራንሶችና እንደ ኢትዮ ቴሌኮም ያሉ የፊንቴክ ተቋማት በአዲሱ አዋጅ መሠረት ተጨማሪ እሴት ታክስ በሚሰጡት አገልግሎቶቻቸው ላይ ጨምረው 15 በመቶ የአገልግሎት ክፍያቸውን አሻሽለው ወደ ሥራ መግባታቸውንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአዲሱ ተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ መሠረት የአገልግሎት ክፍያዎቹ ላይ የዋጋ ጭማሪ መደረጉን ካሳወቁ ባንኮች መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲሆን ትናንት በይፋ እንዳስታወቀው ባንኩ በሚሰጣቸው አገልግሎቶቹ ላይ ተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከትናንት ጀምሮ መተግበሩን ገልጿል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/133998/**

## በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች

**8. Railway, port infrastructure network upgrade needs USD 2.6bln: Ministry report**

**The reporter: October 5, 2024**

Experts at the Ministry of Transport and Logistics estimate the cost of a series of projects aimed at improving logistics infrastructure and upgrading the country's railway networks at more than USD 2.6 billion.

A Ministry report dubbed 'Reform Prospects for Ethiopia's Railway and Surface Transport' published this week provides an overview of the resources needed for diversifying port outlets in neighboring countries, upgrading the Ethio-Djibouti Railway, introducing railway safety standardization, and other capacity-building works.

**https://www.thereporterethiopia.com/42141/**

**9. Comms Authority revises bandwidth fee rates**

**The reporter: October 5, 2024**

The Ethiopian Communications Authority (ECA) has introduced a new directive that determines license fees and annualized fees for different operators in the telecom, internet, mobile and radio station service sectors.

The directive sets the base value for mobile frequency bands, ranging from 967,200 birr to 3.5 million birr per Megahertz (MHz) per year. The fee varies based on variations in frequency bandwidth.

The annual frequency usage fee to be paid by licensed telecommunications operators for the frequency bands assigned to mobile services will be subject to phased payment installed under four phases, according to the directive.

A licensee will be obliged to pay a quarter of the total fee in its first year of operation and settle the fee in its entirety by the fourth year.

Annual usage fees for frequency bands assigned to broadcasting vary from 2,000 birr to a little over 20,000 birr with community radio stations paying the least and commercial radio stations paying the most. Public radio stations will be charged a little over 14,000 birr.

https://www.thereporterethiopia.com/42128/#google_vignette

10.**Ethiopia's Cultural Outfits Have Potential to Become Global Hub for Fashion, Apparel**

**ENA: October 5/2024**

The intertwining of fashion with Ethiopia's rich cultural and historical tapestry enhances the country's global identity.

With a strategic focus and contemporary design, Ethiopia's cultural outfits have the potential to become globally recognized, positioning the country as a global hub for fashion and apparel," according to the Ministry of Foreign affairs

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5246240

11.**COMESA Urges African Countries to Enhance Access to ICT Services**

**ENA: October 4/2024**

The Common Market for Eastern and Southern Africa (COMESA), a regional economic organization in Africa, urged African countries to implement targeted policies to improve access to information and communications technology (ICT) services on the continent.

COMESA Director for Infrastructure and Logistics Bernard Dzawanda made this remark at the start of a meeting on enhancement of governance and enabling environment in ICT program in Lusaka, the Zambian capital, according to Xinhua.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5236864

**12.Ethiopia Expresses Commitment to Expand Trade, Investment with Indonesia**

**ENA: October 4/2024**

Ethiopia is fully committed to exploring avenues for capacity building, investment promotion, and trade facilitation with Indonesia, according to Ministry of Foreign Affairs.

The Embassy of the Republic of Indonesia in Ethiopia held a diplomatic reception in Addis Ababa on Thursday to commemorate the 79th Anniversary of the Independence of the Republic of Indonesia.

Speaking at occasion, Ambassador Negus Kebede, Director General for Middle East, and Asia Pacific at the Ministry of Foreign Affairs said the diplomatic relation between Ethiopia and Indonesia has flourished from time to time.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5236359

13. **Ethiopia central bank releases $175m to forestall forex crisis**

**EAST AFRICA NEWS: OCTOBER 05 2024**

The National Bank of Ethiopia (NBE) has released $175 million into the economy to forestall a foreign currency crisis linked to fuel-related payments falling due in the coming months, and which could erode the economic dividend arising from the International Monetary Fund (IMF)-backed financial sector reforms.

The banking regulator said in a statement on October 3 that the funds would help cover the foreign exchange needs of the Ethiopian Petroleum Supply Enterprise (EPSE), the primary importer of fuel and fuel products in Ethiopia.

**https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business**